የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ የ2012 በጀት ዓመት የግማሽ ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

ታህሳስ 30፣ 2012 ዓ.ም

እንጅባራ — ኢትዮጵያ

የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ 1፡ የ2012 ዓ.ም የ1ኛው ሴሚስተር መደበኛ ተማሪዎች ቁጥር 3
ሰንጠረዥ 2፡ የ2012 ዓ.ም የ1ኛው ሴሚስተር መደበኛ ተማሪዎች መጠነ-ማቋረጥ 3
ሰንጠረዥ 3፡ የ2012 ዓ.ም የእሁድና ቅዳሜ (weekened) ፕሮግራም ተማሪዎች መረጃ..... 4
ሰንጠረዥ 4፡ የ2012 ዓ.ም የክረምት /summer/ ፕሮግራም ተማሪዎች መረጃ 5
ሰንጠረዥ 5፡ በየኮሌጁ ያሉ መምህራን ቀጥር..... 5
ሰንጠረዥ 6፡ የመምህራን ቁጥር በአካዳሚክ ደረጃ..... 5
ሰንጠረዥ 7፡ የአውትሶርስ ሠራተኞች ቁጥር 6
ሰንጠረዥ 8፡ ጠቅላላ የሠራተኞች ቁጥር 6
ሰንጠረዥ 9፡ የተሰጠ የማህበረሰብ አግልግሎት ዝርዝር 13
ሰንጠረዥ 10፡ ዓመታዊ የበጀት ዕቅድና አፈጻጸም ንጽጽር 14
ሰንጠረዥ 11፡ የ2012 ዓ.ም የ2ኛው ሩብ ዓመት የዕቅድ ክንውን ንጽጽር 18

የሰንጠረዥ ማውጫ i
መግቢያ 1
ክፍል አንድ፡ አህዛዊ መረጃዎች እና የዝግጅት ምዕራፍ ተግባራት 3
1.1. አህዛዊ መረጃዎች 3
1.2. የዝግጅት ምዕራፍ ተግባራት 7
ክፍል ሁለት፡ የትግበራ ምዕራፍ ተግባራት 8
2.2. አሠራር፣ አደረጃጀት እና መልካም አስተዳደር 8
2.2.1. የልማት ሠራዊት ግንባታ 8
2.2.2. የመልካም አስተዳደር ሥራዎች እና የባለዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ተፈጻሚነት 8
2.2.3. የዩኒቨርሲቲውን ገፅታ ግንባታ 10
2.2.4. አሠራርና አደረጃጀትን የሚያሻሽሉ መመሪያዎች 10
2.2.5. የሰው ኃብት አቅምን ማሳደግ 10
2.3. መደበኛ ትምህርት 11
2.4. ተከታታይ ትምህርት 11
2.5. የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት 12
2.6. በጀት አስተዳደርና አጠቃቀም 14
2.7. ቤተ-መጽሐፍትና ዶክመንቴሽን 15
2.8. ህንጻ የግንባታ ፕሮጀክቶች 15
2.10. የግቢ ውበት፣ ጽዳት፣ ትራንስፖርትና ደህንነት 16
2.11. የተማሪዎች እንቅስቃሴ 17
2.12. የዕቅድ አፈጻጸም ንጽጽር 18
ክፍል ሦስት፡ የማጠቃለያ ምዕራፍ ሥራዎች 24
3.1. በዕቅድ አፈፃፀም የታዩ ጠንካራ ጎኖች 24
3.2. በዕቅድ አፈፃፀም የታዩ ደካማ ጎኖች 25
3.3. ያጋጠሙ ችግሮች 25
3.4. የተወሰዱ የመፍትሔ ርምጃዎች 25
1.1. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች 25
አባሪዎች 28

መግቢያ

ትምህርት ብቃት ያለው፣ በራሱ የሚተማመንና ሥራ ፈጣሪ ዜጋ ለማፍራት እንዲሁም በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ የሚወስን ማህበረሰብ ለመገንባት እጅግ አስፈላጊና ወሳኝ ግብዓት መሆኑ የሚታወቅ ጉዳይ ነው፡፡ የኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት በዕውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት የተገነቡ፣ ለሰላም መጠበቅ፣ ለሁለንተናዊና ፈጣን ልማት መረጋገጥ እንዲሁም ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና ለመልካም አስተዳደር መስፈን የድርሻቸውን የሚወጡ ብቁ ዜጎችን የማፍራት ተልዕኮ አለው፡፡

ትምህርት በሥነ-ጥበብ፣ በማህበራዊ ሣይንስ እንዲሁም በተፈጥሮ ሣይንስና ቴክኖሎጂ የበለፀገ ዜጋ ለመፍጠር፣ ልማትን ለማፋጠን እና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የማይተካ ሚና ይጫወታል፡፡ ስለሆነም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ማስፋፋትና ማበልጸግ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡ የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲም በዚሁ ዓላማ የሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽ ዕቅድ አካል ሆኖ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 352/2008 የተመሠረተ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ነው፡፡

ያለህን ዕምቅ አቅም ለይና ተጠቀም የሚል መሪ ቃል ያለው የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ *በእውቀት፣ በክህሎት፣ በአመለካከትና በሥነ-ምግባር ብቁ የሆኑ ሥራ ፈጣሪ ምሩቃንን ማፍራትና ሀገራዊ ብሎም ዓለም አቀፋዊ ፋይዳ ያላቸው ሣይንሳዊ ጥናትና ምርምሮችን በማካሄድ ለማህበረሰቡ አገልግሎት መስጠትን* ተልዕኮ አድርጎ ይንቀሳቀሳል፡፡ ዩኒቨርሲቲው *በ2022 ዓ.ም በኢትዮጵያ ተመራጭ በአፍሪካ ታዋቂ ዩኒቨርሲቲ የመሆን* ራዕይንም አንግቧል፡፡

ዩኒቨርሲቲው በአሁኑ ወቅት በ4 ኮሌጆችና በ25 ትምህርት ክፍሎች ውስጥ 218 መምህራንና 12 ቴክኒካል ረዳቶች የማስተማር ሥራውን እየፈጸመ ይገኛል፡፡ እንዲሁም 272 የአስተዳደር፣ 619 የአውትሶርስ እና 4 የፕሮጀክት ሠራተኞች ያሉት ሲሆን በአጠቃላይም 1,125 ሠራተኞች በዩኒቨርሲቲው ውስጥ እየሠሩ ይገኛሉ፡፡

ዩኒቨርሲቲው በዚህ ግማሽ ዓመት ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር መልካም ግንኙነት በመፍጠር፣ ሰላሙ ተጠብቆ እንዲቀጥል በማድረግ እና ለምርምር ተግባር ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ረገድ አመርቂ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ በተለያዩ የሀገሪቱ ዩኒቨርሲቲዎች በተከሰቱ የጸጥታ ችግሮች ጋር በተያያዘ የተወሰነ ግርግር በእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ ውስጥም ተከስቶ የነበረ ቢሆንም የሀገር ሽማግሌዎች፣ መምህራን፣ የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር፣

የጸጥታ አካሉና የተማሪዎች አደረጃጀቶች ባደረጉት ርብርብ ከአራት ቀናት በኋላ ወደመደበኛው መማር ማስተማር መግባት ተችሏል፡፡

ዩኒቨርሲቲው በዚህ ግማሽ ዓመት ለዳንግላና ለጃዊ ሆስፒታሎች እያንዳንዳቸው 7 ሚሊዮን ብር የሚያወጡ ልዩ ልዩ የህክምና መሣሪያዎችን ሂማን ብሪጅ ከተባለ ግብረ ሰናይ ድርጅት ጋር በመተባበር ለግሷል፡፡

በዚህ የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በ2012 ግማሽ ዓመት በዕቅድ ተይዘው የተከናወኑ ተግባራት፣ የግቦች አፈጻጸም፣ ያጋጠሙ ችግሮች፣ የተሰጡ መፍትሔዎችና በቀጣይም የባለድርሻ አካላትን ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ተዳሰዋል፡፡

ክፍል አንድ፡ አሀዛዊ መረጃዎች እና የዝግጅት ምዕራፍ ተግባራት

1.1. አሀዛዊ መረጃዎች

ሰንጠረዥ 1፡ የ2012 ዓ.ም የ1ኛው ሴሚስተር መደበኛ ተማሪዎች ቁጥር

ተ.ቁ	ኮሌጅ	የ1ኛ ዓመት ተማሪዎች			የ2ኛ ዓመት ተማሪዎች			የ 3ኛ ዓመትዓመት ተማሪዎች			ጠቅላላ መደበኛ ተማሪዎች		
		ወ	ሴ	ድ	ወ	ሴ	ድ	ወ	ሴ	ድ	ወ	ሴ	ድ
1	ግብርና፣ ምግብና ዐየር ንብረት ሳይንስ	-	-	-	148	116	264	137	147	248	285	263	548
2	ተፈጥሮና ቀመር ሣይንስ	421	490	911	152	86	238	91	101	192	664	677	1341
3	ማህበራዊና ሰብዓዊ ሳይንስ	525	367	892	136	104	240	82	72	154	743	543	1286
4	ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ	-	-	-	245	152	397	249	133	182	494	285	779
ድምር		946	857	1803	681	458	1,139	559	453	1012	2186	1768	3954

ሰንጠረዥ 2፡ የ2012 ዓ.ም የ1ኛው ሴሚስተር መደበኛ ተማሪዎች መጠነ-ማቋረጥ

ፆታ	መጠነ-ማቋረጥ						
	አሳውቀው ያቋረጡ /withdrawal/				ሳያሳውቁ ያቋረጡ /dropout/		
	1ኛ ዓመት	2ኛ ዓመት	3ኛ ዓመት	ጠቅላላ	1ኛ ዓመት	2ኛ ዓመት	3ኛ ዓመት
ወንድ	10	9		19	64	11	-
ሴት	13	-		13	66	5	-
ድምር	23	9		32	130	16	-

ሰንጠረዥ 3፡ የ2012 ዓ.ም የእሁድና ቅዳሜ (weekened) ፕሮግራም ተማሪዎች መረጃ

		1ኛ ዓመት			የ2ኛ ዓመት		
		ወንድ	ሴት	ድምር	ወንድ	ሴት	ድምር
ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ							
1	አካውንቲንግና ፋይናንስ	158	127	285	95	63	158
2	ኢኮኖሚክስ	111	33	144	30	9	39
3	ማኔጅመንት	318	389	707	105	96	201
ንዑስ ድምር		587	548	1135	230	168	398
የማህበራዊና ሰብዓዊ ኮሌጅ							
1	የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ - የአማርኛ ቋንቋ	28	34	62	51	116	167
2	የእንግሊዝኛ ቋንቋና ሥነ-ጽሑፍ	-	-	-	39	10	49
3	ጂኦግራፊና አካባቢ ጥናት	-	-	-	30	14	44
4	የሥነ-ዜጋ እና ሥነ-ምግባር ጥናት	-	-	-	24	23	47
ንዑስ ድምር		28	34	62	144	163	307
የተፈጥሮና ቀመር ሣይንስ ኮሌጅ							
1	ባዮሎጂ	46	17	63	57	35	92
2	ሒሳብ	-	-	-	22	5	27
3	ኮምፒዩተር ሳይንስ	101	38	139	127	40	167
4	ስፖርት ሳይንስ	-	-	-	81	54	135
5	አይቲ	48	20	68	-	-	-
ንዑስ ድምር		195	75	270	287	134	421
ጠቅላላ ድምር		810	658	**1468**	661	465	**1126**

ሰንጠረዥ 4፡ የ2012 ዓ.ም የክረምት /summer/ ፕሮግራም ተማሪዎች መረጃ

		ወንድ	ሴት	ድምር
ማህበራዊ ሳይንስና ሰብዓዊ ኮሌጅ				
1	ጅኦግራፊና የአካባቢ ጥናት	208	133	341
2	የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሁፍ	145	333	478
3	እንግሊዘኛ ቋንቋና ሥነ-ጹሁፍ	208	112	320
4	የሥነ-ዜጋና ሥነ-ምግባር	129	114	243
	ንዑስ ድምር	690	692	1382
የተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ ኮሌጅ				
1	ስፖርት ሳይንስ	346	162	508
2	ሒሳብ	261	77	338
3	ባዮሎጂ	278	211	489
4	ኬሚስትሪ	156	52	208
5	ፊዚክስ	77	15	92
	ንዑስ ድምር	1118	517	1635
ጠቅላላ ድምር		*1808*	*1209*	*3,017*

ሰንጠረዥ 5፡ በየኮሌጁ ያሉ መምህራን ቁጥር

ኮሌጅ	ወንድ	ሴት	ድምር	የሴቶች ድርሻ በ%
ማህበራዊና ሰብዓዊ ሳይንስ ኮሌጅ	56	13	67	13.4
ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ	31	3	34	8.8
የተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ	51	16	67	23.8
ግብርና፣ ምግብና ዐየር ንብረት ሳይንስ	37	11	48	27.4
ድምር	175	43	218	19.7

ሰንጠረዥ 6፡ የመምህራን ቁጥር በአካዳሚክ ደረጃ

ተ.ቁ	ደረጃ	ወንድ	ሴት	ድምር	ምርመራ
1	ፕሮፌሰር	1	-	1	
2	ተባባሪ ፕሮፌሰር	-	-	-	
3	ረዳት ፕሮፌሰር	5	1	6	
4	ሌክቸረር	159	41	200	
5	ረዳት ሌክቸረር	1	1	2	
6	ረዳት ምሩቅ I	6	-	6	
7	ረዳት ምሩቅ II	3	-	3	
	ድምር	175	43	218	
	የመምህራን የትምህርት ደረጃ ስብጥር ሬሽዮ	5:91.7:2.7			
8	ሴኔየር ቴክኒካል	12	-	12	
	ጠቅላላ ድምር	187	43	230	

ሰንጠረዥ 7፡ የአውትሶርስ ሠራተኞች ቁጥር

ተ.ቁ	የሥራ መደቡ መጠሪያ	ወንድ	ሴት	ድምር
1	የካምፓስ ፖሊስ (ጥበቃ ሠራተኞች)	109	28	137
2	ጽዳት ሠራተኛ	3	76	79
3	ጽዳትና መስተንግዶ ሠራተኛ	23	51	74
4	ወጥ ቤት	25	56	81
5	ቲከር (የተማሪ ምግብ ተቆጣጣሪ)	8	6	14
6	የተማሪ መኝታ ተቆጣጣሪ (ፕሮክተር)	24	18	42
7	የመኝታ ክፍል ጽዳት	4	72	76
8	እንጀራ ጋጋሪ	14	62	76
9	አትክልተኛ	6	18	24
10	ዳቦ ቤት	14	2	16
ጠቅላላድምር		230	389	619

ሰንጠረዥ 8፡ ጠቅላላ የሠራተኞች ቁጥር

የሥራ ዘርፍ	ወንድ	ሴት	ድምር	የሴቶች ድርሻ በ%
የአስተዳደር ሠራተኞች	154	118	272	43.3
የፕሮጀክት ሠራተኞች	4	-	4	0
አውት ሶርስ ሠራተኞች	230	389	619	62.8
መምህራን	175	43	218	19.7
ሲኒየር ቴክኒካል	12	-	12	0
ድምር	575	550	1,125	48.8

1.2. የዝግጅት ምዕራፍ ተግባራት

- የ2011 በጀት ዓመት የዕቅድ የአፈጻጸም ሪፖርት በዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ቦርድ ጸድቋል፡፡ መምህራን እና ሌሎች ሠራተኞች በውይይት አዳብረውታል፡፡
- የ2012 በጀት ዓመት ዕቅድ ተዘጋጅቶ ከሚመለከታቸው አካላት፣ ከመምህራንና ከአስተዳደር ሠራተኞች ጋር ውይይት ተደርጎበት በቦርዱ ጸድቋል፡፡ በሁሉም መምህራንና ሠራተኞች በየሥራ ዘርፉ የእርስ በእርስ ግምገማ ተደርጎ ጠንካራ ጎኖች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ፣ ደካማ ጎኖች እንዲታረሙ ተደርጓል፡፡ ተማሪዎችም መብትና ግዴታቸውን እንዲያውቁ የሚያስችል ውይይት ተካሂዷል፡፡
- ለአንደኛው ወሰነ ትምህርት አስፈላጊ ዝግጅቶች ሁሉ ተደርገዋል፡፡
- ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ልዩ ልዩ ሥልጠናዎች ተሰጥተዋል፤ ውይይቶችም ተደርገዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል፡-
    - የከፍተኛ ትምህርት የማስተማር ሥነ-ዘዴ (HDP) እና የካሪክለም ሥልጠና ለ22 ወንድና ለ7 ሴት አዳዲስ መምህራን ለ3 ቀናት ተሰጥቷል፡፡
    - በሰላማዊ መማር ማስተማር ዙሪያ፣ በከፍተኛ ትምህርት ፎኖተ-ካርታ ዙሪያ፣ በተማሪዎች መብትና ግዴታ እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው ህግና ደንብ ላይ ለሁሉም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብና ተማሪዎች ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡
    - ከካቶሊክ ሪሊፍ ሰርቪስ ፕሮግራምና USAID ጋር በመተባበር ለ25 መምህራን በምርምር ፕሮፖዛል አጻጻፍ፣ አሠራርና አተገባበር ዙሪያ ለ8 ቀናት ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡
    - ከዳልሀውሲ ዩኒቨርሲቲ /ካናዳ/ ጋር በመተባበር ለ86 መምህራን የ2ኛ ዙር የስታስቲክስ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡
    - ለ40 መምህራንና ለ20 ተማሪዎች ከወሎ ዩኒቨርስቲ በመጡ ተመራማሪ በማህበረሰብ አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ሥልጠናና ልምድ ልውውጥ ተደርጓል፡፡ 20 የሚሆኑ የአስተዳደር ሠራተኞችም ወደተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ሄደው ልምድ ቀስመዋል፡፡
    - ለ555 አንደኛ ዓመት ተማሪዎች የአንድ ቀን የህይወት ክህሎት ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

ክፍል ሁለት፡ የትግበራ ምዕራፍ ተግባራት

2.2. አሠራር፣ አደረጃጀት እና መልካም አስተዳደር

2.2.1. የልማት ሠራዊት ግንባታ

- በአካዳሚክ ዘርፍ 24 በአስተዳደር ዘርፍ 30 በድምሩ 54 የልማት ቡድኖችና 146 የኮኦፐሬቲቭ ለርኒንግ (የ1ለ5) አደረጃጀቶች አሉ፡፡ የተደራጁ ሠራተኞች ብዛት ወንድ 424 ሴት 390 ድምር 814 ናቸው፡፡ በአጠቃላይ መደራጀት ከሚገባቸው 882 ሠራተኞች መካከል 814 (92.3%) ተደራጅቷል፡፡ ተማሪዎችን በተመለከተ 60 የልማት ቡድን እና 382 የ1ለ5 የተደራጁ ሲሆን ወንድ 1,274 ሴት 1,041 ድምር 2,315 ተማሪዎች ተደራጅተዋል፡፡
- አቅጣጫ ጠቋሚ በየሥራ ክፍሎች ተለጥፈዋል፤ የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ ወጥቷል፡፡

2.2.2. የመልካም አስተዳደር ሥራዎች እና የባለዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ተፈጻሚነት

መልካም አስተዳደር፡- አግልግሎቶች የመልካም አስተዳደር እሴቶችንና መርሆዎችን መሠረት አድርገው እየተፈጸሙ ናቸው፡፡ ከዘር፣ ከቀለም፣ ከጾታ እና ከሃይማኖት ልዩነት በጸዳ መልክ ማንኛውም አገልግሎት እንዲሰጥ በዩኒቨርሲቲው ፕሬዘዳንት ለሁሉም ሠራተኛ መልዕክት ተላልፎ በዚሁ መሠረት እየተሠራ ነው፡፡ ብልሹ አሠራር ሲከሰትም ተጠያቂ የሚያደርግ አሠራር በመኖሩ የንብረት ጥፋት የፍትሐብሔር ክስ በፍርድ ቤት ክርክር ተደርጎ ለዩኒቨርሲቲው ተወስኗል፡፡ ሐሰተኛ የሥራ ልምድ በአቀረበ አንድ ሠራተኛ ላይም የዲሲፕሊን ዕርምጃ ተወስዳል፡፡ በአጠቃላይ በተቋሙ የሰው ኃይል ስምሪትና በግዥ ሂደት የሥነ-ምግባር ግድፈት እንዳይፈጠር ክትትል ተደርጓል፡፡ መንግስት ያወጣቸው አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና የአሠራር ማንዋሎች በየደረጃው ባሉ የሥራ ክፍሎች ተግባራዊ መሆናቸው እየተረጋገጠ ሥራዎች እየተሠሩ ናቸው፡፡

የምግብ አገልግሎት፡- የምግብ ጥሬ ዕቃዎችም ሆነ የምግብ ዝግጅቱን የተማሪ ተወካዮች እንዲያረጋግጡ በመደረጉ ያለምንም ቅሬታ የምግብ አገልግሎቱ እየተሰጠ ይገኛል፡፡ ከዚህ ቀደም በተማሪዎች ምግብ ግብዓቶች ላይ በታየው የጥራት መዋዠቅ ምክንያት ሽሮ፣ በርበሬና እንጀራ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ እንዲዘጋጅ በመደረጉ በመጠንም ሆነ በጥራት የተሻለ አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል፡፡ አሁንም የተማሪዎችን የምግብ ጥራት አገልግሎት ለማሻሻል 3 ወፍጮ በተመረጠ ቦታ ተተክሎና 2 የጤፍ ማበጠሪያ ተዘጋጅቶ አገልግሎት

እየሰጠ ነው፡፡ የተማሪዎች መዝናኛ በጥራት አገልግሎት እንዲሰጥ ክትትል እየተደረገ ነው፡፡ የግቢው ሠራተኞች መዝናኛ በጥራት አገልግሎት እንዲሰጥ የዩኒቨርሲቲው ብድርና ቁጠባ ህብረት ሥራ ማህበር እያንቀሳቀሰው ይገኛል፡፡

የመኝታ አገልግሎት፡- 7 ባለአራት ፎቅ ሕንጻዎችና በ3 ጊዜያዊ ሕንፃዎች ንጹህና ቁሳቁስ የተሟላላቸው 863 ዶርሞች አሉ፡፡ የዶርም ተማሪ ጥምርታ ዕቅድ 1፡4 ሲሆን አፈጻጸሙ 1፡4.6 ላይ ነው፡፡ በዶርሞች አካባቢ ምንም ዓይነት የጸጥታ ችግር እንዳይኖር ብሎክ፣ ፍሎር እና የዶርም ተጠሪ ተመድቧል፡፡ በተማሪዎች ማደሪያ አካባቢ 2 የልብስ ማጠቢያ ላውንደሪዎች አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡

የህክምና አገልግሎት፡- በክሊኒክ ደረጃ ለተማሪዎች በተገቢው መንገድ የህክምና አገልግሎት እየተሰጠ ሲሆን በሆስፒታል ደረጃ ለሚሰጡ አገልግሎቶች የሪፈራል ቅደም ተከተሎችን ለታካሚዎች በማስረዳት ቀልጣፋ አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ ለ139 ምግብ ሠራተኞች የንጽህና አጠባበቅ ትምህርት ተሰጥቶ ሙሉ የጤና ምርመራ ተደርጓል፡፡ መድሃኒት በ378,548.00 ብር ተገዝቷል፡፡ በግዥ የማይገኙ 10,500.00 ብር የሚያወጡ መድሐኒቶች ከተለያየ ጤና ተቋማት በትውስት በቢን ካርድ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡

የተማሪዎች ዲስፕሊን፡- በዲሲፕሊን መመሪያ ዙሪያ ለዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡ በዲሲፕሊን ግድፈት 15 ተማሪዎች ተከሰው ነበር፡፡ ከእነዚህ ውስጥ 1 የክረምት ተማሪ ሙሉ በሙሉ ከትምህርት እንዲሰናበት ሲወስን 1 መደበኛ ተማሪ ደግሞ ለአንድ ዓመት ከትምህርት የመታገድ ውሳኔ ተሰጥቶበታል፡፡ 13ቱ ተማሪዎችም ገና ውሳኔ ያልተሰጣቸው ናቸው፡፡ ክስ ያልተመሰረተባቸው በቃል በምክር የታለፉ 14 ተማሪዎችም አሉ፡፡

ሴቶች፣ ሕጻናትና ወጣቶች፡- በ2011 በጀት ዓመት ትምህር ዘመን 3.75 እና ከዚያ በላይ ውጤት ያስመዘገቡ 33 ሴት ተማሪዎችና 4 ነጥብ ያስመዘገቡ 7 ወንድ ተማሪዎች በድምሩ 40 ከፍተኛ ውጤት ለስመዘገቡ ተማሪዎች የምስክር ወረቀት ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም ፎቶና ውጤታቸውን የያዘ ባነር ተዘጋጅቶ በዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ቦታዎች ላይ ተቀምጧል፡፡

የአካል ጉዳተኞችን በተመለከተ፡- ለ6 አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በትምህርት ምርጫ፣ በማደሪያ፣ በመማሪያ ክፍል፣ በላይበራሪና በኢንተርኔት አጠቃቀም ዙሪያ ቅድሚያ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ለእያንዳንዳቸውም በየወሩ የ400 ብር ድጋፍ እየተደረገላቸው ይገኛል፡፡

ኤች አይ ቪ /ኤድስ፡- ዓለም አቀፍ የኤድስ ቀን ‹‹ማህበረሰቡ የለውጥ አቅም ነው›› በሚል መፈክር በተለያዩ ዝግጅቶች የተከበረ ሲሆን ቫይረሱ አሁን ያለበት የስርጭት ሁኔታ ላይም ግንዘቤ ተፈጥሯል፡፡

2.2.3. የዩኒቨርሲቲውን ገፅታ ግንባታ

የዩኒቨርስቲውን ገጽታ የሚገነቡ 5 ዜናዎች ተሰርተዋል፡፡ ይህም በዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች አለመረጋጋት ምክኒያት ይናፈሱ የነበሩ አፍራሽ አሉቧልታዎች አፍርሷል፡፡ ተማሪዎች ቆሻሻ አመለካከትን እናጽዳ በሚል መፈክር የጽዳት ዘመቻ አድርገዋል፡፡ የአማራ ክልል የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ፎረም በእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ ተካሂዷል፤ የሚዲያ ሽፋንም እንዲያገኝ ተደርጓል፡፡

የዩኒቨርሲቲዎች ዓመታዊ አዲናስ የሚል መጽሔት እና የዓመቱን ዋና ዋና ክንውኖች ያካተተ ዓመታዊ መጽሔት በአማርኛና በእንግሊዘኛ በብሮሸር መልክ ተዘጋጅቶ ለግቢው የሥራ ክፍሎች ተሰራጭቷል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ዓመታዊ ስታትስቲክስ መጽሔት ለህትመት ቀርቧል፡፡ የተማሪዎች አቀባበልና የተለያዩ የማህበረሰብ አገልግሎቶች በፎቶና በቪዲዮ ዶክመንት ተሰንደዋል፡፡ የዩኒቨርሲቲውን ድህረ-ገጽና ማህበራዊ ሚዲያ በመጠቀም ልዩ ልዩ የተቋሙ ክንውኖች፣ ማስታወቂያዎች የማስተዋወቅ ሥራ ተሰርቷል፡፡

2.2.4. አሠራርና አደረጃጀትን የሚያሻሽሉ መመሪያዎች

የዩኒቨርሲቲውን አሠራር የሚያሻሽሉ የሚከተሉት የአሠራር መመሪያዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

1. **የነፃ ትምህርት ዕድል መመሪያ**፡- የአስተዳደርና የአካዳሚ ሠራተኞችና ቤተሰቦች የነፃ ትምህርት ዕድል መመሪያ ተዘጋጅቶ ጸድቋል፡፡
2. **የሹመት መመሪያ**፡- የመካከለኛ አመራር ምርጫ፣ ሹመት/ ምደባ ለመደንገግ የወጣ መመሪያ ጸድቋል፡፡

ተነሺ አርሶ አደሮች በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ ያለፈቃድ በሚያደርጉት መተላለፍ እና በግቢው ውስጥ በሚፈጽም አንዳንድ የንብረት ስርቆት አስፈላጊው ህጋዊ እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡

2.2.5. የሰው ኃብት አቅምን ማሳደግ

ዩኒቨርሲቲው 272 የአስተዳደር፣ 619 የአውትሶርስ፣ 4 የፕሮጀክት ሠራተኞች እንዲሁም 218 መምህራንና 12 ሲኒየር ቴክኒካል ረዳቶች በድምሩ 1,125 ሠራተኞች አሉት፡፡

አስፈላጊ የሆኑ ክፍት የሥራ መደቦችን ለማሟላት በማስታወቂያ ጋብዞ በሜሪት ሥርዓት በማወዳደር፣ በደረጃ ዕድገት፣ በዝውውርና በቅጥር ስምሪት ተፈጽሟል፡፡

የትምህርት ሥልጠና፡- በሦስተኛ ዲግሪ ትምህርት 14 ወንድና 2 ሴት መምህራን ትምህርታቸውን በሀገር ውስጥ በመከታተል ላይ የሚገኙ ሲሆን የ2ኛ ዲግሪ ትምህርትን በተመለከተ 1 በውጭ ሀገርና 3 በሀገር ውስጥ የሚሰለጥኑ መምህራን አሉ፡፡ በመጀመሪያ ዲግሪም 3 ወንድ መምህራን እየተማሩ ናቸው፡፡

2.3. መደበኛ ትምህርት

የመደበኛ ተማሪዎች ቅበላና ምዝገባ በአካዳሚክ ካሊንደሩ መሠረት በተቀላጠፈና በተሳካ መልኩ ተከናውኗል፡፡ ዩኒቨርሲቲው በ2012 ዓ.ም 1,803 አዲስ ተማሪዎችን እና 2,268 ነባር ተማሪዎችን በድምሩ 4,071 የመደበኛ ፕሮግራም ተማሪዎችን ተቀብሏል፡፡ የ3ኛ ዓመት ተማሪዎች ቁጥር 559 ወንድ እና 453 ሴት ሲሆን በድምሩ 1,012 ተማሪዎች ሲሆን በዚህ ዓመት መጨረሻ ለመጀመሪያ ጊዜ ማስመረቅ እንጀምራለን፡፡

ሁሉም የዩኒቨርሲቲውና የአካባቢው ማህበረሰብ በከፍተኛ ተሳትፎ ተማሪዎችን በድምቀት ተቀብሎ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ናቸው፡፡ ተማሪዎች የወጪ መጋራት ውል እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ የመጀመሪያ ቀን የመጀመሪያ ክፍል የሚለው መርህ ተፈጻሚ ሆኗል፡፡ የመማር ማስተማር ሒደቱ በትምህርት ክፍል ካውንስል፣ በአካዳሚክ ካውንስልና በከፍተኛ አመራሮች ለሚነሱ ጉዳዮች አፋጣኝ ውሳኔ እየተሰጠ የመማር ማስተማር ሒደቱ ሠላማዊና ጤናማ ሆኖ ቀጥሏል፡፡ ተማሪዎች በግቢ ውስጥና በአቅራቢያው በሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች በመሔድ የተግባር ትምህርት ወስደዋል፡፡ ለሆቴል ተማሪዎች የተግባር ትምህርት መማሪያ ወርክ ሾፕ እየተቋቋመ ነው፡፡

2.4. ተከታታይ ትምህርት

የክረምት /summer/ መርሃ-ግብር፡- የክረምት ትምህርት ለመጀመር የአዋጭነት የዳሰሳ ጥናት ተደርጎ በሴኔት ከጸደቀ በኋላ 1808 ወንድ እና 1209 ሴት በድምሩ 3017 ተማሪዎችን ተቀብሎ በ2 ኮሌጆችና በዘጠኝ ትምህርት ክፍሎች ትምህርት እየተሰጠ ነው፡፡ የመምህራን ዕጥረት ባለባቸው ትምህርት ክፍሎች ከውጭ መምህራንን በመቅጠር ተሸፍኗል፡፡ ተማሪዎች እንደየፍላጎታቸው ግቢ ውስጥ ዶርም ይዘው ምግብ ዩኒቨርሲቲው እንዲያቀርብላቸው የሚልፈልጉትንና የማይፈልጉትን በመለየት ተከናውኗል፡፡

በእሁድና ቅዳሜ /weekend/ መርሃ-ግብር፡- በእሁድና ቅዳሜ መርሃ-ግብር 810 ወንድና 658 ሴት በድምሩ 1,468 የ1ኛ ዓመት ተማሪዎች እንዲሁም የ2ኛ ዓመት ተማሪዎች ወንድ 661 ሴት 465 በድምሩ 1,126 ተማሪዎች ትምህርታቸውን በመከታተል ይገኛሉ፡፡

2.5. የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት

የምርምር ሥራዎች፡- የምርምር ሥራዎችን የሚገመግም ቴክኒካል ቡድን ተቋቁሞ በ2011 በጀት ዓመት የተጀመሩ የምርምር ሥራዎች ያሉበት ደረጃ ከተገመገመ በኋላ 25% በጀት እንዲለቀቅና መጠናቀቅ የሚገባቸው ሥራዎች ተጠናቀው ሪፖርት እንዲያደርጉ እንዲሁም ለ2012 የሚቀጥሉት 50% በጀት እንዲለቀቅላቸው ተደርጓል፡፡ ለ2012 ዓ.ም አዲስ የምርምር ፕሮፖዛል እንዲቀርብ ማስታወቂያ ወጥቶ 70 የሚደርሱ አዳዲስ የምርምር ፕሮፖዛሎች ቀርበዋል፡፡ ከቀረቡት በግምገማ የጸደቁት 41 ፕሮፖዛሎች ሲሆኑ 50% በጀት ለማስለቀቅ ዝግጅት እየተደረገ ነው፡፡ በአርሶ አደር ማሳ ላይ ተዘርተው የነበሩ የግብርና የምርምር ምርቶች ተሰብስበዋል፡፡ ISSD ፕሮጀክት ጋር በመተባበር የሚሰሩ የምርምር ሥራዎች ክትትል እየተደረገ ሲሆን የፋይናንስ ሪፖርትም ተደርጓል፡፡ ለምርምርና ለማስተማር አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ ስክሪንና ግሪን ሀውስ እንዲሁም አንድ የድንች ማጎንቆያ ግንባታ ተጀምሯል፡፡

የማህበረሰብ አገልግሎት፡- በዚህ ግማሽ ዓመት 10 የማህበረሰብ አገልግሎት በመስጠት 1,294 የማህበረሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 4 የማህበረሰብ አገልግሎት ተሰጥቷል፤ 92 የማህበረሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ በማህበረሰብ አገልግሎት የተሳተፉ ወንድ 14 ሴት 1 በድምሩ 15 መምህራን ናቸው፡፡

ዩኒቨርስው ትኩረት ሰጥቶ ከሚሰራባቸው የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎች ውስጥ ለልማት ተነሺ አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ፕሮፖዛል በመምህራን ተቀርጾ በምርምርና በማህበረሰብ አገልግሎት ካውንስል ርዕሶች ተገምግመዉ ከተመረጡ በኋላ በኮሌጅ በተመረጡ ገምጋሚ ኮሚቴና በካዉንስሉ ሦስት /3/ ፕሮፖዛሎች አስተያየት ተሰጥቶባቸው ለፕረዘንቴሽን ያለፉት እንዲያስተካክሉ ተሰጥቷል፡፡ በየኮሌጆች ሦሰት አባላትን የያዘ የማህበረሰብ አገልግሎት የቁጥጥርና የገምጋሚ ኮሚቴ አባላት ተዋቅሯል፡፡

ሰንጠረዥ 9፡ የተሰጠ የማህበረሰብ አግልግሎት ዝርዝር

ተ.ቁ	የድጋፍና ሥልጠናው ርዕስ	የስልጠናው ቦታ	ሥልጠናው የወሰደው ጊዜ	የሰልጣኞች ብዛት			የተሳተፉ መምህራን			ምርመራ
				ወ	ሴ	ድ	ወ	ሴ	ድ	
1	Application of GIS and Rs for Urban Planning and Land Management for Awi Zone Municipal Workers and urban planer	እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ	5	28	7	35	14	1	15	ጆኦግራፊና አካባቢ ጥናት፣ የእንግሊዘኛ ቋንቋና ሥነ-ጹሁፍ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል ተሳትፈዋል፡፡
2	የንባብ ልምድና የማንበቢያ አውድን ምስረታ	አገው ምድር መሰናዶ ት/ቤት	2	10	16	26				
3	በአዊ ዞን የጎልማሶች ትምህርት አተገባበር ላይ ለጎልማሶችና ለአመቻቾች ስልጠናና ድጋፍ ማድረግ	እንጅባራ ከተማ	3	5	8	14				
4	Giving English Language Training to Banja Shikudad Woreda Governmental Primary School English Teachers	እንጅባራ (ማቡክ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት)	4	5	13	18				
ድምር				48	44	92				

ሴሚናር፡- ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ 6 ሴሜናር፣ የተፈጥሮ ቀመር ሳይንስ ኮሌጅ 2 ሴሚናር በአጠቃላይ 8 ሴሚናሮች ተደርገዋል፡፡

2.6. በጀት አስተዳደርና አጠቃቀም

የ2012 በጀት ዓመት የበጀት ዕቅድ ተዘጋጅቶ በገንዘብና ትብብር ሚኒስቴር 251,267,100 (ሁለት መቶ ሀምሳ አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ስልሳ ሰባት ሺህ አንድ መቶ) ብር ተፈቅዷል፡፡ ከዓመቱ የበጀት ዕቅድ አንጻር የግማሽ ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ብር 80,402,303.01 (32%) ነው፡፡ ከ6 ወር በጀት ዕቅድ ጋር ሲነጻጸር አፈጻጸሙ 52.2% ላይ ነው፡፡

ሰንጠረዥ 10፡ ዓመታዊ የበጀት ዕቅድና አፈጻጸም ንጽጽር

ተ.ቁ	ፕሮግራም	ለ2012 በጀት ዓመት ተስተካክሎ የተመደበ በጀት (ዕቅድ)	የ2ኛ ሩብ ዓመት ዕቅድ	አፈጻጸም	
				በአሃዝ	በመቶኛ
1	ለሥራ አመራርና አስተዳደር	95,598,200.00	62,637,798	31,356,572.13	50%
2	መማር ማስተማር	105,328,900.00	66,764,440	36,602,440.59	54.8%
2	ለተማሪዎች	35,000,000.00	13,800,000	10,602,441.50	76.8%
3	ለጥናትና ምርምር አገልግሎት	10,340,000.00	6,900,002	1,638,436.10	23.7%
4	ለማማከርና ማህበረሰብ አገልግሎት	5,000,000.00	3,727,975	202,412.69	5.4%
ድምር		251,267,100.00	153,830,215 (61.2%)	80,402,303.01	52..2%

የዓመቱ የውስጥ ገቢ ዕቅድ ብር 6,000,000.00 (ስድስት ሚሊዮን ብር) ከተከታታይ ተማሪዎች ለመሰብሰብ ታቅዶ 12,526,900.00 ብር ተሰብስቧል፡፡ ከዚህ ውስጥ 8,975,257.00 ብር ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

ግዥን በተመለከተ፡- ከአንድ አቅራቢ፣ በውስን ጨረታና በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ በ32,857,855.12 ብር (የጠቅላላ ወጪውን 21.3%) የተለያዩ ዕቃዎች ግዥ ተፈጽሟል፡፡ ንብረት ቆጠራ ተደርጎ የተገኘ ጉድለት የለም፡፡

2.7. ቤተ-መጽሐፍትና ዶክመንቴሽን

ዲጂታል ላይበራሪ በ100 ኮምፒዩተሮች ተደራጅቶ ኢንተርኔትና ዋይ ፋይ አግልግሎት እየሰጠ ሲሆን ሶፍት ኮፒ መጽሐፍትም ከኮሌጆች ተሰብስቧል፡፡ በአለፈው ዓመት የነበሩ መጽሐፍትን በመቁጠር፣ ያለውን ክፍተት ለመሸፈን ከፖሊ-ቴዳ ኢንተርፕራይዝ ጋር ውል ተይዞ 6,750 መጽሐፍት ታትሞ ገቢ ሆኗል፡፡ በቤተ-መጽሐፍቱ አጠቃላይ 39,980 ዋቢ እና ማጣቀሻ መጽሐፍት አለ፡፡ የመጽሐፍ ተማሪ ጥምርታ ዕቅድ 1፡15 ሲሆን አፈጻጸም 1፡10 ነው፡፡ ቤተ-መጻሕፍቱ የተቀመጠውን የተማሪዎችን ውጤት ከፍ ለማድረግና ኢላማው ግብ እንዲመታ የ24 ሰዓት የተሟላ አገልግሎት እየሰጠ ነው፡፡ ለተቋሙ የምርምር ቋት (Institutional Repositary) ክፍል ተዘጋጅቶ 15 ኮምፒዩተሮች ገብተዋል፡፡ ለጥናትና ምርምር የሚሆኑ ጆርናሎች በየዲፓርትመንታቸው ተለይተው አገልግሎት እየሰጡ ነው፡፡

2.8. ህንጻ የግንባታ ፕሮጀክቶች

በሁለተኛው ዙር ለተማሪዎች መኝታ አገልግሎት የሚውል ሦስት ባለ አራት ፎቅ፣ ሦስት ጊዜያዊ ዶርሚተሪና አንድ ለላውንደሪ አገልግሎት የሚውል ሕንፃ በ105,507,756 ብር በ4 ተቋራጮች ተገንብቷል፡፡ የ3ቱ ባለ አራት ፎቅ የመኝታ አገልግሎት ሕንጻ ግንባታ ላይ የላውንደሪ፣ የተማሪዎች ጊዜያዊ ማደሪያ ህንጻና የሁለት ባህላዊ ማብሰያ ቤቶች ግንባታ አፈጻጸም 99.88% ሲሆን ተጠናቆ ርክክብ ተፈጽሟል፡፡ በ3ኛው ዙር በ29,718,385 ብር እየተገነባ ያለው ባለ 4 ፎቅ የተማሪዎች መማሪያ ክፍል ያለበት ደረጃ 76.85% ላይ ነው፡፡

2.9. መሠረተ ልማት

የውኃና የመብራት አቅርቦት፡- በውኃ አቅርቦትና ፍሳሽ ሠራተኞች ክትትል እየተደረገ 24 ሠዓት የንጹህ ውኃ አገልግሎት ይሰጣል፡፡ የውኃ ፓምፕ ኮንትሮል ቦርድ ተበላሽቶ ጥገና ተደርጓል፡፡ መብራት በሁሉም ሕንጻዎችና በዋና መንገዱ ላይ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ መብራት በሚጠፋበት ወቅትም ጀነሬተሮችን በመጠቀም የዩኒቨርሲቲው መማር ማስተማር ሥራና ሌሎችም ተግባራት ሳይቋረጡ ቀጥለዋል፡፡ በኮንትራክተር የሚሠራው

የመብራት ግንባታ በ52,887,556.74 ብር የሚገነባ ሲሆን አፈጻጸሙ ያለበት ደረጃ 87.07% ላይ ነው፡፡

ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽ ቴክኖሎጂ፡- ፈጣን የኢንተርኔትና ዋይፋይ አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል፡፡ የኔት ወርክ መሠረተ-ልማት ሽፋንን በማሳደግ በሁሉም ሕንፃዎች የኢንተርኔት አገልግሎት ተደራሽ ሆኗል፡፡ ለተማሪዎች ዲጅታል ላይበራሪ፣ ኢንፎርሜሽን ሪፖዝታሪ ክፍል፣ ሲስኮ ኔትወርኪንግ ማሰልጠኛ እና ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የኢንተርኔት አገልግሎት መስጫ የኔት ወርክ ዲዛይን ሥራ ተሰርቷል፡፡ በዩኒቨርሲቲው የሚገኙ የኔት ወርክ ዕቃዎች በኮምፒዩተር ዳታ ቤዝ ተይዘዋል፡፡

ለአዲስ መምህራን በዩኒቨርሲቲው ዶሜን ኢሜል አካውንት ተሰጥቷል፡፡በሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር የተዘጋጀውን የመረጃ መሰብሰቢያ ሶፍትዌር ለተወሰቡ ባለሙያዎች የማስተዋወቅ ሥራ የተሰራ ሲሆን በቀጣይም ለሁሉም ለሚመለከተው ክፍል የማስተዋወቅና መረጃውን ወደ ሶፍትዌሩ የማስገባት ሥራ ለመስራት ታቅዷል፡፡

መንገድ፡- በዩኒቨርሲቲው ግቢ 9.701 ኪ.ሜ ዋና መንገድ በ66,260,280 ብር ለመገንባት በተቋራጭ ውል ተይዞ የዲች ሥራ፣ ጠጠርና አስፓልት በመሙላት ላይ ይገኛል፡፡ የውስጥ ለውስጥ የእግረኛ መንገድ 3.60 ኪ.ሜ በ34,958,964 ብር ለመገንባት ታቅዶ የጠጠርና ኮብል ስቶን ሙሌት እየተሠራ ይገኛል፡፡ እነዚህ የአፈጻጸም ደረጃዎች የተለኩት ሥራው ከሚጠይቀው የበጀት መጠን ጋር ሲሆን ይህም ሥራው ያለበትን ደረጃ በቀጥታ የሚነግረን ነው፡፡

ሳኒተሪ፡- በኮንትራክተር በ45,430,457 ብር እየተሠራ ያለው ሴኒተሪ ያለበት የአፈጻጸም ደረጃ 86.43% ላይ ነው፡፡

2.10. የግቢ ውበት፣ ጽዳት፣ ትራንስፖርትና ደህንነት

የግቢ ውበት፡- የዩኒቨርሲቲውን ግቢ በአትክልት በማስዋብ ጽዱና አረንጓዴ የማድረግ ሥራው በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ አረንጓዴ ለማልበስ በዕቅድ የተያዘው ቦታ ጠቅላላ ስፋት 60,000 ካሬ ሜትር ሲሆን ከዚህ ውስጥ 52,115 ካሬ ሜትር የሚሆነው በአረንጓዴ ተሸፍኗል፡፡ በዚህም ሳርና የአበባ ተክሎችን የመትከል፣ የማጨድ /የማስተካከል/፣ ውኃ የማጠጣትና ተጨማሪ እንክብካቤዎችን የማድረግ ሥራ ሲሠራ

ቆይቷል፡፡ በተጨማሪም በዚህ የበጀት ዓመት ብቻ 9,000 ችግኞች ተተክለው እንክብካቤ እየተደረገላቸው ይገኛል፡፡ ሀምሌ 22 ቀን 2011 ዓ.ም 2000 ችግኞች ተከላ ተካሒዷል፡፡ በችግኝ ተከላው ላይ መምህራን፣ የአስተዳደር ሠራተኞች፣ ተማሪዎችና ሌሎች አካላት ተሳትፈውበታል፡፡ የእንሰሳት ሳይንስ፣ የዕፅዋት ሳይንስ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ፣ የተፈጥሮ ኃብት አያያዝ ሰርቶ ማሳያ (ሞዴል) ችግኝ ጣቢያ ተሰርቷል፡፡

ትራንስፖርት፡- በዩኒቨርሲቲው ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ 7 የመንግስት ተሽከርካሪዎች ያሉ ሲሆን የተሽከርካሪ እጥረትን ለመቅረፍ 2 አውቶቢሶች፣ 1 ሚኒባስና 1 ፒክአፕ በድምሩ 4 መኪኖችን በመከራየት አገልግሎት እየሰጡ ናቸው፡፡ ሁለት ባጃጅ ተገዝቶ የምግብ ቤትና የወፍጮ ቤት ሥራው ቀልጣፋ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ አንድ ሞተር ሳይክል ተገዝቶ አስቸኳይ የጥገና ሥራዎችን ለማከናወን አገልግሎት እየሰጠ ነው፡፡

ሠላምና ደህንነት፡- በአውትሶርስ ሠራተኝነት ያሉት የካምፓስ ፖሊሶች የግቢውን ሰላምና ደህንነት በማስጠበቅ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፆ አድርገዋል፡፡ ሰላም እና ጸጥታን ለማስጠበቅ የተማሪዎች ህብረትን ጨምሮ ያሉ ልዩ ልዩ የተማሪዎች አደረጃጀት እና መላው የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ትልቅ ሚና ተጫውተዋል፡፡

2.11. የተማሪዎች እንቅስቃሴ

ክበባት፡- በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ተማሪዎች እንደየዝንባሌያቸው በንቃት የሚሳተፉባቸው የተለያዩ አሥር ክበባት አሉ፡፡ እነዚህም የሥነ-ውበት፣ የበጎ አድራጎት፣ የፀረ-ኤድስ፣ የሥርዓተ-ፆታ፣ የሥነ-ጥበብ፣ የሥነ-ምግባር፣ የሠላም ፎረም፣ የአገርህን ዕወቅ፣ የስፖርት እና የተማሪ ፖሊስ ናቸው፡፡ የክበባት አመራሮች የክበባት፣ ማህበራትና በጎ አድራጎት ዘርፍ ኮሚቴ አባላት እንዲሆኑ ተደርጓል፤

ስፖርትና መዝናኛ፡- ሦስት የቲቪ ክፍልና አንድ የዲ.ኤስ.ቲቪ. አገልግሎት መስጫ ክፍል በማዘጋጀት ተገቢ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡

የተማሪዎች ህብረት፡- ህብረቱ ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ተዋቅሮ የራሱን መተዳደሪያ ደንብ አውጥቶ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል፡፡ አደረጃጀቱ 3 ዋና የሥራ አስፈጻሚና 11 የየዘርፉ ሥራ አስፈጻሚ አባላት ያሉት ሲሆን ለሰላማዊ መማር ማስተማር ከፍተኛ አስተዋጽዖ አድርጓል፡፡

2.12. የዕቅድ አፈጻጸም ንጽጽር

ሰንጠረዥ 11፡ የ2012 ዓ.ም የ2ኛው ሩብ ዓመት የዕቅድ ክንውን ንጽጽር

ዕይታ	ተቋማዊ ግቦች	የአፈፃፀም መለኪያዎች		የ2012 ዓ.ም ዒላማ/ Target	2ኛ ሩብ ዓመት	ክንውን
ደንበኛ (20%)	የዩቨርሲቲውን ገፅታ መገንባት	የማስተዋወቅ ስራ ብዛት በቁጥር				
		በህትመት ሚዲያ		3	1	1
		ኢሌክትሮኒክስ ሚዲያ (ሬዲዮና ቴሌቭዥን)		10	2	5
		መድረኮች		2	1	-
	የደንበኛና አጋር አካላትን እርካታ ማሻሻል	የደንበኞች እርካታ በመቶኛ		75	-	-
		የአጋር አካላት እርካታ በመቶኛ		75	-	-
		የቅሬታ መጠን መቀነስ በመቶኛ		2.5	3.5	-
	ደንበኛና አጋር አካላትን ቁጥር ማሳደግ	የተማሪዎች ዲሲፕሊን ግድፈት በመቶኛ		1.5	0	0.02
		የመመረቅ ምጣኔ በመቶኛ				
		መጠነ ማቋረጥ በመቶኛ (withdrawal & dropout)		1.5	0.25	-
		መጠነ ስንብት በመቶኛ		2	1	-
		መደበኛ ተማሪዎች ብዛት በቁጥር	አዲስ ተማሪዎች	2,000	2,000	1,803
			ነባር ተማሪዎች	2,268	2,268	2,268
			ድምር	4,268	4,268	4071

		ተከታታይ (የክረምት እና የቅዳሜና እሁድ)	5,517	የክረምት	3,017
				ቅዳሜና እሁድ 1ኛ ዓመት	1,468
				ቅዳሜና እሁድ 2ኛ ዓመት	1,126
				ድምር	5,611
		የተሰጠ የማህበረሰብ አገልግሎት ብዛት በቁጥር	20	10	4
		የማህበረሰብ አገልግሎት ያገኙ ሰዎች ብዛት በቁጥር	2,594	1,294	92
		የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ስርፀት ብዛት በቁጥር	3	1	-
		የጸደቀ የጥናትና ምርምር ፕሮፖዛል ብዛት በቁጥር	30	30	41
		በታወቁ ጆርናሎች የጥናትና ምርምር ውጤቶችን ማሳታም በቁጥር	50	20	-
		የሀገር ውስጥ አጋር አካላት በቁጥር	3	1	-
		የውጭ ሀገር አጋር አካላት በቁጥር	3	1	-
ፋይናንስ (10%)	የሀብትና በጀት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሻሻል	የበጀት አጠቃቀም በመቶኛ	100	61.2	52.2
		በአግባቡ ተይዞ ጥቅም ላይ የዋለ ንብረት በመቶኛ	100	-	ንብረት ቆጠራ ተደርጎ የተገኘ ጉድለት የለም
		የከይዘን ፍልስፍናን ተግባራዊ ያደረጉ የሥራ ክፍሎች ብዛት በመቶኛ	80	60	60
	የውስጥ ገቢን ማሳደግ	የገቢ መጠን በብር	6 ሚሊዮን	-	12,526,900.00
		የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ የተከናወነ ተቋማዊ ግምገማ ብዛት በቁጥር	1	-	1

የውስጥ አሰራር (40%)	የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን ማሻሻል	የካሪኩለም ግምገማ ያካሄዱ የትምህርት ክፍሎች ብዛት በቁጥር	28	-	28
		የሥራ አፈጻፀም ግምገማ ያደረጉ የሥራ ክፍሎች በቁጥር	55	55	20
		አገልግሎታቸውን በስታንዳርድ አስደግፈው የሚሰጡ የሥራ ክፍሎች ብዛት በቁጥር	55	55	
		የቅሬታ አፈታት ሥርዓት ሰነድ በቁጥር	2	2	-
		የተፈቱ ቅሬታዎች በመቶኛ	100	100	
		የማበረታቻ ሥርዓት ሰነድ በቁጥር	2	2	-
		ማበረታቻ የተደረገላቸው ሰራተኞች ብዛት በቁጥር	83	30	-
	የውስጥ ተግባቦትን ማጎልበት	ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የተፈጠሩ የውይይት መድረኮች በቁጥር	2	1	1
		የዩኒቨርሲቲ ካውንስል የተካሄዱ መድረኮች	4	1	-
		በዓመቱ በቦርድ የተከናወኑ የዕቅድ አፈፃጸም ግምገማዎች በቁጥር	4	1	1
		የውጤት ተኮር ሥርዓት የተገበሩ ሥራ ክፍሎች በቁጥር	55	55	38
		የኮኦፐሬቲቭ ለርኒንግ ተግባራዊ የተደረገባቸው የሥራ ክፍሎች በቁጥር	55	55	20
		ዓመታዊ የስታትስቲካዊ መረጃ መጽሄት (Bulletin) በቁጥር	2	-	በህትመት ሂደት ላይ
		ለሴት መምህራን የተዘጋጀ ስልጠና ብዛት በቁጥር	5	1	-

	የባለ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ተፈጻሚነትን ማሻሻል	ለሴት የአስተዳደር ሠራተኞች የተዘጋጀ ስልጠና ብዛት በቁጥር	4	1	-
		ለሴት ተማሪዎች የተዘጋጀ ስልጠና ብዛት በቁጥር	5	1	1
		ልዩ ዕገዛ የተደረገላቸው ሴት ተማሪዎች በመቶኛ	*100*	*100*	*100*
		ዕገዛ የተደረገላቸው የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች በመቶኛ	*100*	100	100
		የሴቶች የአመራር ተሳትፎ በከፍተኛ፣ በመካከለኛና በዝቅተኛ ደረጃ በመቶኛ	20	13	14.5
መማ ማርና ዕድገት (30%)	የሰው ኃብትን አቅም ማሳደግ	የመምህራን የትምህርት ደረጃ ስብጥር በሬሽዮ (የመጀመሪ ዲግሪ ፡ 2ኛዲግሪ ፡ 3ኛ ዲግሪ)	4.7:93.3:1.5	4.7:93.3:1.5	5:91.7:2.7
		ለ2ኛ ዲግሪ ትምህርት የሚሄዱ መምህራን በቁጥር	4	-	3
		ለ3ኛ ድግሪ ትምህርት የሚሄዱ በቁጥር	39	-	16
		የከፍተኛ ትምህርት የማስተማር ስነዘዴ (HDP) ስልጠና የወሰዱ መምህራን በቁጥር	30	30	29
		›ምህር-ተማሪ ጥምርታ	1:30	1:30	1:19
		የቴክኒካል ረዳቶች ብዛት በቁጥር	6	-	-
		ለትምህርት የሚላኩ ቴክኒካል ረዳቶች በቁጥር	3	-	-
		አዲስ የተቀጠሩ የአስተዳደር ሰራተኞች ብዛት በቁጥር	92	-	47
		ዩኒቨርሲቲው የትምህርት ዕድል የሚሰጣቸው አስተዳደር ሠራተኞች በቁጥር	15	15	5
		ለአስተዳደር ሰራተኛ የተሰጠ የአጭር ጊዜ ስልጠና ብዛት በቁጥር	8	2	1

		ለመምህራን የተሰጠ የአጭር ጊዜ ስልጠና ብዛት በቁጥር	9	2		5
		የልምድ ልውውጥ ያገኙ የአስተዳደር ሠራተኞችና የስራ ክፍል ኃላፊዎች ብዛት በቁጥር	90	30		20
	የቴክኖሎጂ ተደራሽነትና ሽግግርን ማጎልበት	አውቶሜት የተደረጉ የሥራ ክፍሎች ብዛት በቁጥር	4	2		
		በዲጅታል ላይበራሪ የተደራጁ ኮምፒዩተሮች ከተማሪ ብዛት አንጻር ያለው ጥምርት	1፡40	1፡40		1፡4.7
		ሞዴል (በአይ ሲቲ የታገዙ) እና ዘመናዊ መማሪያ ክፍሎች በመቶኛ	100	100		100
	ፋሲሊቲ በዓይነትና በብዛት ማሳደግ	የተሟላ ላቦራቶሪዎች ያሏቸው አካዳሚክ ክፍሎች በቁጥር	42	-		17
		ዋና የማጣቀሻ መጽሐፍት -ተማሪ ጥምርታ	1፡15	1፡15		1፡10
		የመማሪያ ክፍል-ተማሪ ጥምርታ	1፡60	1፡60		1፡50
		የዶርም-ተማሪ ጥምርታ	1፡4	1፡4		1፡4.6
		የዋና መንገድ ግንባታ በመቶኛ	-			173.12
		የውስጥ ለውስጥ መንገድ ግንባታ በመቶኛ	100			44.1
		ኤሌክትሪክ ዝርጋታ በመቶኛ	100			87.07
		ሳኔቴሪ በመቶኛ	100			86.43
		ጀኔሬተር የተዳረሰባቸው ህንጻዎች ብዛት በቁጥር	11	7		4
		የስልክ መስመር በቁጥር	40	-		4
		የግቢ ዙሪያ አጥር በሽቦ በመቶኛ	100	60		-
		የህንፃ ግንባታ በዕቅዱ መሰረት በመቶኛ	100	90	የ2ኛው ዙር	99.88

					የ3ኛው ዙር	61.26
		ጽዱና አረንጓዴ ግቢ በመቶኛ	100	25		86.85
		ስፖርትና መዝናኛ አገልግሎት በመቶኛ	50	-		-
	የሰራተኞችን እርካታ መጨመር	የረኩ ሠራተኞች በመቶኛ	80	-		-
	አሰራርና አደረጃጀትን ማሻሻል	አዲስ የተዘጋጁ የአፈጻጸም መመሪያዎች ብዛት በቁጥር	2	1		2
		የተሻሻሉ መመሪያዎች ብዛት በቁጥር	4	10		-
		የተሻሻሉ የሥራ መደቦች ብዛት በቁጥር	30	5		-
		አዳዲስ የተፈጠሩ የሥራ መደቦች ብዛት በቁጥር	10	80		6
		የኮኦፐራቲቭ ለርኒንግ መመሪያን ተግባራዊ ያደረጉ ቡድኖች በመቶኛ	80	2		76.6
	መረጃ አያያዝና አስተዳደርን ማሻሻል	በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የታገዘ መረጃ የሚጠቀሙ የስራ ክፍሎች ብዛት በቁጥር	6	-		

ክፍል ሦስት፡ የማጠቃለያ ምዕራፍ ሥራዎች

በበጀት ዓመቱ በዕቅድ ተይዘው የተከናወኑ ግቦችንና ዋና ዋና ተግባራትን የአፈጻጸም ስኬት ለመለካት የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡ የክትትልና ግምገማ ሥርዓቱ ዕቅድ አፈጻጸም ሂደት ላይ ችግር የሚፈጥሩ ጉዳዮችን ለመለየትና በየጊዜው የመፍትሔ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ቦርድም ሆነ በየደረጃው ያለው አመራር ግምገማዎችን በማድረግ የዩኒቨርሲቲው ሥራዎች ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆኑ እያደረጉ ናቸው፡፡

የግንባታና መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች በትምህርት ሚኒስቴር ሥር ቢሆኑም በበጀት ዓመቱ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ዕቅድ መሠረት እንዲጠናቀቁ የክትትልና ግምገማ ሥራ ተሰርቷል፡፡

የተከታታይ ምዘና በወቅቱ እየተሰጠ መሆኑን በየጊዜው ክትትል እየተደረገ ነው፡፡ በየትምህርት ክፍሎች የፈተና ኮሚቴዎችን በማቋቋም ፈተናዎች እንዲገመገሙ ተደርጓል፡፡ ለተማሪዎች የአካዳሚክ አዳቫይዘር ተመድቧል፡፡ የትምህርት ክፍለ ጊዜያት እንዳይባክኑ ጥረት የተደረገ ሲሆን በተለያዩ ምክንያት የባከኑትም በወቅቱ እንዲካካሱ ተደርጓል፡፡ ለሴት ተማሪዎችና ውጤታቸው ዝቅተኛ ለሆኑ ተማሪዎች የቲቶሪያል /ማጠናከሪያ/ ትምህርት ተሰጥቷል፡፡

የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ቦርድ አንድ ጊዜ ተሰብስቦ የ2011 ዓ.ም በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸምና የ2012 ዓመታዊ ዕቅድ ገምግሞ አጽድቋል፡፡

3.1. በዕቅድ አፈፃፀም የታዩ ጠንካራ ጎኖች

ሰላማዊ የመማር ማስተማር ሒደት መኖሩ፡- ከሀገራዊው ወቅታዊ ሁኔታ ጋር በተገናኘ እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ ውስጥም ቀላል ግርግል የተፈጠረ ቢሆን ጉዳዩን በአጭር ጊዜ መፍታትና ወደመነኛ መማር ማስተማር ተመልሰናል፡፡

ጠንካራ የተማሪዎች ህብረት መኖሩ፡- የተለያዩ ግብዓቶችን ፈጥኖ በማሟላት እና ከተማሪ ተወካዮች ጋር ተከታታይ ውይይት በማድረግ ችግሮች በወቅቱ እየተፈቱ መማር ማስተማሩ በተሳካ ሁኔታ ቀጥሏል፣ የዚህ አንዱ ምክንያትም የተማሪዎች ህብረት ጠንካራ በመሆኑ ነው፡፡

ደማቅ የተማሪዎች አቀባበል፡- በተማሪዎች አቀባበል ላይ ሁሉም የዩኒቨርሲቲውና የአካባቢው ማህበረሰብ ከፍተኛ ተሳትፎ አድርገዋል፡፡

ግቢውን አረንጓዴ የማድረግ ሂደት፡- የዩኒቨርሲቲውን ግቢ ውበትና ንጽህና በተለይም ግቢውን አረንጓዴ የማልበስ ሥራ በአመርቂ ሁኔታ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ አረንጓዴ እንዲሆን ከተያዘው የግቢው የቆዳ ስፋት ውስጥ ከ87 በመቶ በላይ ተግባራዊ ሆኗል፡፡

የኢንተርኔት አገልግሎት መኖሩ፡- በየቢሮዎቹ የኢንተርኔት አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል፡፡

የምርምርና የማህበረሰብ አገልግሎት ተጠናክሮ መቀጠሉ፡- ተቋሙ አዲስ መሆኑ ሳይገድበው ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት በሜጋ ፕሮጀክት መርህ እየተሠራ ይገኛል፡፡

3.2. በዕቅድ አፈፃፀም የታዩ ደካማ ጎኖች

- የኔትወርክ ዝርጋታ በተለያዩ የኔትወርክ ዕቃዎች ዕጥረት ምክንያት አለመጠናቀቁ፤
- የስፖርት ሜዳ ዝግጅት መዘግየቱ፤

3.3. ያጋጠሙ ችግሮች

- የ2ኛው ዙር ሕንጻ ግንባታ መዘግየቱ፤
- የእንጅባራ ቻግኒ የአስፓልት መንገድ እስከ ዩኒቨርሲቲው ወሰን ጫፍ ድረስ መንታ መንገድ ባለመሆኑ ምክንያት ለተማሪዎች እንቅስቃሴ ስጋት መፍጠሩ፤
- የግዥ መጓተት በመኖሩ የቢሮና የትምህርት ቁሳቁስ አቅርቦት ላይ ውስንነት መኖሩ፤

3.4. የተወሰዱ የመፍትሔ ርምጃዎች

- የተማሪዎች ማደሪያ ችግርን ለማቃለል ጊዜያዊ የተማሪዎች ማደሪያ ተገንብቷል፡፡
- በማዕከላዊ መንግስት ቃል በተገባው መሠረት መንገዱ መንታ ሆኖ እንዲሠራ ለሚመለከታቸው አካላት ተደጋጋሚ የማሳወቅ ሥራና ክትትል እየተደረገ ነው፡፡

1.1. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

- ተደጋጋሚ የሆነ የመብራት መቆራረጥ፤
- የመምህራን መኖሪያ ቤት ጉዳይ፤
- የፕሮጀክት በጀትን ከማስተዳደር ጋር በተገናኘ የሚደርሰው ከፍተኛ የግንባታ መጓተት እና የተማከለ የፕሮጀክት የበጀት አስተዳደር መኖር፤
- የመንግስት የግዢ ሥርዓት የተንዛዛ መሆኑና አቅራቢዎችም በውላቸው መሠረት ያለመፈጸም ችግሮች መታየታቸው፤

- ተነሺ አርሶ አደሮች ካሳ የተከፈላቸው ቢሆንም ምትክ ቦታ ተሰጥቷቸው አመነሳታቸው፤
- ዩኒቨርሲቲው አጥር የሌለው መሆኑ፤

አባሪዎች

1) የህዝብ ግንኙነት ሥራዎች

ሀምሌ 22 ቀን 2011 ዓ.ም 2000 ችግኞች ተከላ